# ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር
# የፈራሚዎች ጉባኤ

## የስብሰባ ቃለጉባዔ

መጋቢት 21 ቀን 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

# ዘመን ኢንሹራንስ ኢ.ማ. (በምሥረታ ላይ ያለ)

## የፈራሚዎች ጉባኤ

## ቃለ ጉባኤ ቁጥር 01

1. ጉባኤው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣

   1.1. ቦታ፣ በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል

   1.2. ቀን፣ መጋቢት 21 ቀን 2011 ዓ.ም.

   1.3. ሰዓት፣ ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

   የፈራሚዎች ጉባኤ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 392 እና 395 መሠረት ከጉባኤው ዕለት 15 ቀናት አስቀድሞ ስፊ ሽፋን ባላቸው በሪፖርተር መጋቢት 1 እና 4/2011 ዓ.ም ፣ በካፒታል መጋቢት 1/2011 ዓ.ም፣ በአዲስ ዘመን መጋቢት 4፣5 እና 6/2011 ዓ.ም. በወጡ የጋዜጣ እትሞች እንዲሁም በስልክ እና በአጭር የስልክ መልእክት /'SMS'/ በተደጋጋሚ ጥሪ ተደርጓል፡፡

3. የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት እና በጉባኤው የተገኙ የመሥራች ኮሚቴ አባላት /አደራጆች/፣

3.1. የጉባኤው ጽ/ቤት አባላት፣

| ተ.ቁ. | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | አቶ አማረ ሀበ | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2. | አቶ መስፍን አበበ (ቱሉ ቶኩማ ንግድና ትራንስፖርት ኢ.ማ) | ድምጽ ቆጣሪ |
| 3. | አቶ ኢሳያስ ተስፋዬ (ምናየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር) | ድምጽ ቆጣሪ |
| 4. | አቶ ሰለሞን ደምሌ | የጉባኤው ጸሐፊ |

3.2. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307/3/ መሠረት በጉባኤው የተገኙ መሥራች አባላት

| ተ.ቁ. | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | አቶ አማረ ሃበ | የመሥራች ኮሚቴ ሰብሳቢ |
| 2. | አቶ ሹመቴ ዘርይሁን | አባል |

3. አቶ ዮናስ አምደጽዮን አባል

4. አቶ እሸቱ ወልደኪዳን አባል

ያልተገኙ

1. አቶ ዘለቀ ተስፋየ አባል

3.3. በጉባኤው የተገኙ ታዛቢዎች፣

1. አቶ ሽመልስ አዳሙ ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

2. አቶ ሐጐስ ሰይፉ ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

4. ምልዓተ ጉባኤ፣

4.1. ጠቅላላ የማህበሩ አባላት ብዛት ---- 925

4.2. ጠቅላላ የማህበሩ የተፈረመ አክሲዮን ብዛት --- 22,921

4.3. በስብሰባው የተገኙ አባላት የያዙት የአክሲዮን ብዛት --13,501 ወይም 58.9%

## ዝርዝር አጀንዳና ውይይት

### 1. ድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየምና ማጽደቅ፣

ስብሰባውን ለማካሄድ የምልዐተ ጉባኤው አባላት መሟላታቸውንና ጉባዔውን ለማካሄድ የሚያስችሉ ሕጋዊ ሁኔታዎች ማረጋገጥ በማስፈለጉ ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም አስፈልጓል፡፡ በዚህ መሠረት በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕጋችን ከዚህ በኋላ የንግድ ሕጉ እያልን በምንጠራው አንቀጽ 405 ከፍተኛ አክሲዮን ካላቸውና ፈቃደኛ የሆኑ ባለአክሲዮኖች በቆጣሪነት እንዲሰየሙ የቀረቡትን፣

1ኛ ቱሉ ቶኩማ የንግድና ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ተወካይ አቶ መስፍን አበበ

2ኛ ምናዬ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተወካይ አቶ ኢሳያስ ተስፋዬ

እንዲቀበላቸው ለፈራሚዎች ጉባዔ ቀረበ፡፡በሕጉ መሠረት የቀረቡትን ቆጣሪዎች የፈራሚዎች ጉባዔ በምልአተ ጉባኤው ተቀብሎ አጸደቀ፡፡ የጉባዔውን ጸሐፊነትም አቶ ሰለሞን ደምሴን ጸሐፊ አድርጎ መደበ፡፡ የፈራሚዎች ጉባዔ በንግድ ሕግ አንቀጽ 320/2 መሠረት በድንገተኛ ጉባዔ ድንጋጌ መሠረት መካሄድ እንዳለበት በስብሳቢው በመገለጹ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 425/3/ መሠረት ከማማሽ ያላነሰ መገኘት ስላለበት በንግድ ሕጉ መሠረት የፈራሚ ባለአክሲዮኖች ጉባዔ ምልአተ ጉባዔ መሟላቱን እንዲያረጋግጡ

ሰብሳቢው ለቆጣሪዎች ማሳሰቢያ ሰጡ፡፡ ቆጣሪዎችም በስብሰባው ላይ የተገኙ ባለአክሲዮኖች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የቆጠራውን ውጤት በመመልከትና የምዝገባ ሰነድ ምልከታ በማድረግ ካለው የተፈረመ ጠቅላላ 22,921 አክሲዮን ውስጥ 12070 አክሲዮን ወይም 52.56 በመቶ ድርሻ የያዙ ባለአክሲዮኖች ቆጠራ በተካሄደበት ሰዓት መገኘታቸውን ለጉባዔው ሪፖርት አደረጉ፡፡ በዚህ መሠረት የተገኘው የአክሲዮን ብዛት በሕግ ከተቀመጠው ዝቅተኛ ቁጥር በላይ በመሆኑ ጉባዔውን መቀጠል የሚያበቃ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸው ወደሚቀጥለው አጀንዳ ቀጠሉ፡፡

## 2. ረቂቅ አጀንዳውን ማፅደቅ፤

በመሥራች ኮሚቴው በኩል የቀረበው ረቂቅ አጀንዳዎች መጋቢት 1 እና 4/2011 ዓ.ም. በሪፖርተር ፣ መጋቢት 1/2011 ዓ.ም. በካፒታል እንዲሁም መጋቢት 4፣5 እና 6/2011 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለአራት ጊዜ በተከታታይ የወጡ ከመሆኑም በላይ ለጉባዔው አባላት በዛሬው ቀን ተሰጥተዋል፡፡

የቀረበው ረቂቅ አጀንዳ፣

1. ድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየምና ማጽደቅ
2. ረቂቅ አጀንዳውን ማጽደቅ
3. ማኅበሩን ለማቋቋም ሁኔታዎች መፈጸማቸውን ሪፖርት ማቅረብና በሪፖርቱ ላይ ተወያይቶ መወሰን
4. በረቂቅ መመሥረቻ ጽሑፍና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ተወያይቶ መወሰን ማጽደቅ
5. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307 መሠረት የመሥራቾችን የትርፍ ድርሻ ተወያይቶ መወሰን ማጽደቅ
6. እስከ የካቲት 21/2011 ዓ.ም ድረስ የገቡ ገቢዎችንና ወጪዎች ኦዲት ሪፖርት ማዳመጥና መወሰን
7. ለ2012 በጀት ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራና ከምሥረታ ኦዲት በኋላ የገቡ ገቢዎችንና ወጪዎችን ለመመርመር የሚሰራ የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን ለመወሰን
8. በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መሠረት የዲሬክተሮች ቦርድን ለመሾም
9. የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ማጽደቅ

በዚህ መሠረት የቀረበው ዝርዝር ረቂቅ አጀንዳ ለፈራሚዎች ጉባኤ ቀርቦ በስብሰባው በተገኙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

3. ማኅበሩን ለማቋቋም ሁኔታዎች መፈጸማቸው ሪፖርት ማቅረብና በሪፖርቱ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

- የመሥራች ኮሚቴው ስብሳቢ የምሥረታ ሂደቱን በሚመለከት እንደገለጹት ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የአክስዮን ሺያጩን እስካሁን ከታዩት ልምዶች ሁሉ በተለየ ሁኔታ ባጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ የፈራሚዎች ጉባዔ በዚሁ ኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል ነሐሴ 5/2010 ተካሂዶ እንደነበር፣
- የጉባዔው መካሄድ ተከትሎ ጥቅምት 2 ቀን 2011 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ከስራ ፈቃድ መጠየቅያ ቅጽ ጋር ተያይዞ መግባቱን፣
- ጥያቄውን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተላከው ማስረጃ ተመርኩዞ በሁለት ዐብይ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቆ እንደነበርና ለተጠየቀው ጥያቄ ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም. 3 ገጽ ደብዳቤ ማብራሪያ በጽሁፍ ምላሽ እንደገባ ተገልጿል:: ከብዙ ክትትል በኋላ ብሔራዊ ባንክ ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የመጨረሻውን ውሳኔ ማሳወቁ ተገልጿል::
- የብሔራዊ ባንኩ ውሳኔ በዋናነት የሚያጠነጥነው በመሥራች ኮሚቴ አባላት /አደራጆች/ በኩል የተሰበሰበው ገንዘብ፤የወጡ ወጪዎች እንዲሁም የተሰሩ ስራዎች ኦዲት ተደርገው ለፈራሚዎች ጉባዔ ቀርበው እንዲጸድቁ የሚል ነው::እንዲሁም በንግድ ህጉ አንቀጽ 350(5) መሰረት የዳይሬክተሮች ምርጫ በእያንዳንዱ ዳይሬክተር ድምጽ በመስጠት እንዲከናወን የሚል ሲሆን በተጨማሪም ለፈራሚዎች ጉባዔ አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም አጀንዳዎች ላይ ውይይት እንዲደረግባቸው እና ውሳኔ እንዲተላለፍባቸው የሚል ነው::
- በዚህ መሠረት ለዚህ ስብሰባ የምሥረታው ሂሣብ ኦዲት የተጠናቀቀና ሌሎች ስብሰባው ለማካሄድ አስፈላጊ ዝግጅቶች የተደረጉ ሲሆን የሂሣብ ምርመራ ሪፖርቱን ኦዲተሩ የተያዘለት አጀንዳ ሲደርስ ለጉባዔው የሚያቀርብ መሆኑ ተገልጿል::
- ከዚህ በተጨማሪ በፕሮጀክት ጽ/ቤት በኩል የአዋጭነት ጥናትና ለየሥራ ክፍሎች 13 የሥራ ማንዋሎች የተዘጋጁ ሲሆን ቀሪዎች አራቱ ወደፊት የሚጠናቀቁ ይሆናል::
- ኦዲት እስከተደረገበት እስከ የካቲት 21/2011 ድረስ ያለው የተከፈለ ካፒታል ብር 81,175,000 /ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አምስት ሽህ/ መድረሱን ተገልጿል::

- በቀረበው ሪፖርት ውይይት ተደርጐ በጉባዔው ላይ የተለየ አስተያየት ሳይቀርብ ሪፖርቱ ያለምንም ድምጸ ተአቅቦና ተቃውሞ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

4. <u>በረቂቅ መመሥረቻ ጽሑፍና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ተወያይቶ መወሰንና ማፅደቅ፤</u>

ቀደም ሲል ተደርጐ በነበረው የፈራሚዎች ጉባዔ ሪፖርት ቀርቦ እንደነበረው የተፈረመ ካፒታል ብር 114,605,000/ አንድ መቶ አሥራ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ አምስት ሽህ/ ላይ ለውጥ የሌለው ቢሆንም እስከ መጋቢት 13/2011 ድረስ የተከፈለ ካፒታሉ ብር 81,540,000 /ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሽህ/ በመድረሱ በዚህ መሠረት የተስተካከለ ሲሆን የተፈረመው ካፒታል ውስጥ ቀሪ ያለባቸው ባለአክሲዮኖች ይኸ ጉባዔ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአሥራ አምስት ወራት ውስጥ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው ማሻሻያ ተደርጐበት ቀርቧል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል በነበረው የፈራሚዎች ጉባዔ ወቅት ለሁሉም ባለአክሲዮኖች ተሰራጭቶ ከነበረው የመመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በብሔራዊ ባንክ በኩል በተሰጡ የማስተካከያ ሃሣቦች መሠረት የቀረቡ የኢዲቶሪያልና የመሠረታዊ አሳቤዎች ተካተው በሁለት ገጽ ቀርቧል፡፡ ባለአክሲዮኖችም በቀረበው የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከተወያዩበት በኋላ ድምጽ እንዲሰጡ ተደርገው ያለምንም ድምጸ ተአቅቦና ተቃውሞ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

5. <u>በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307 መሠረት የመሥራቾችን የትርፍ ድርሻ ተወያይቶ መወሰንና ማፅደቅ፤</u>

በአክሲዮን መግለጫው ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307 በመሥራችነት ከተገለጹት መካከል የመሥራቾች ስብሰባ እስኪካሄድ ድረስ አክሲዮን የገዙና እንዲሁም በአክሲዮን መግለጫው ላይ በመፈረም የመሥራችነት ሥራውን በኃላፊነት ወስደው የማቋቋሙን ተግባር በመሥራት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት በአክሲዮን መግለጫው ላይ እንደተገለጸው የተከፋዩን መጠን በፈራሚ ባለአክሲዮኖች ጉባዔ ይወሰናል ይላል፡፡ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307/2/ እና 307/3/ መሠረት እንደተገለጸው የተከፋዩን እስከ ስት ዓመት የሚቆይና ከተገኘው ትርፍ እስከ ሃያ በመቶ ያልበለጠ የሚፈቀድ በመሆኑ ከዚህ ቀደም በተደረገው የፈራሚ ባለአክስዮኖች ጉባኤ ቀርቦ ያለምንም ተቃውሞ ጸድቆ የነበረው አጀንዳ ዛሬም እንደገና በአጀንዳነት ለፈራሚ ባለአክሲዮኖች

በድጋሚ ለውሳኔ ቀረበ፡፡ በዚህ መሠረትም በአንቀጽ 307/2/ ለተጠቀሱት ፈራሚ ባለአክሲዮኖች አሥር በመቶ እንዲሁም በአንቀጽ 307/3/ ለተጠቀሱት መሥራች ኮሚቴ አባላት አሥር በመቶ እንዲከፈል የቀረበው ሃሣብ ያለምንም ድምጸ ተአቅቦና ተቃውሞ በአንቀጽ 322/3/ መሠረት አምስቱን የመሥራች ኮሚቴ ባለአክሲዮኖች ሳይጨምር በስብሰባው ላይ በተገኙ ሌሎች ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

## 6. እስከ የካቲት 21/2011 ዓ.ም ድረስ ያለው የምሥረታ ገቢዎችና ወጪዎች ኦዲት ሪፖርት ማዳመጥና መወሰን

ኦዲተሩ እስከተጠቀሰው ቀን ድረስ የተፈረመ ካፒታል ብር 114,605,000/አንድ መቶ አሥራ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ አምስት ሺህ/ የተከፈለ ካፒታል ደግሞ ብር 81,175,000/ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ/ መድረሱን፣ የመቋቋሚያ ወጪ/ Establishment cost/ ብር 2,556,268/ሁለት ሚሊዮን አምስት አምሣ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ስምንት ብር/ የተደረገ መሆኑንና ጠቅላላ ሀብቱ 91,633,115/ዘጠና አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ አንድ መቶ አሥራ አምስት/ መድረሱን በኦዲት ሪፖርቱ አብራርቷል፡፡ ኦዲተሩ ሪፖርቱን ካቀረበ በኋላ መድረኩ ለጥያቄ ክፍት ሆኖ የታየ የጐላ ችግር አላየንም የሚል በመቅረቡ ያልጐላው ችግር ምንድን ነው የሚል ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ኦዲተሩም የጐላ ችግር የሚባለው ማጭበርበር ወይም ሌላ ሆን ተብሎ የተሰራና ኩባንያው የሚጐዳ /material facts/ ሲሆን ከዚህ ውጪ ግን ያልጐላ የሚለው በኦዲት አሠራር የተለመደ አገላለጽ በመሆኑ እንጂ የተለየ ነገር አልነበረም በማለት ገልጸዋል፡፡ ገንዘቡ የት ባንክ ነው የተቀመጠው የሚለው በኦዲተሩ ማብራሪያ ተስጥቶበታል፡፡ ሌሎች ጥያቄዎች እንዲቀርቡ ቢጠየቅም ባለመቅረቡ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የድጋፍ ድምጽ ተጠይቆ ያለምንም ድምጸ ተአቅቦና ተቃውሞ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

## 7. 2012 በጀት ዓመታዊ ሂሣብ ምርመራና ከምሥረታ ኦዲት በኋላ የገቡ ገቢዎችና ወጪዎችን ለመመርመር የሚሰራ የውጪ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን ለመወሰን

በንግድ ሕጉ በተገለጸው መሠረት የኩባንያውን የውጭ ኦዲተሮችን መሾም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ጉባዔ ሥልጣን ሲሆን የፍርድ ቤቱ ጽ/ቤቱ ከተቋቋመ መስከረም 2/2010 ጀምሮ የምሥረታ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንዲሁም በ2011 ዓ.ም. ተፈላጊውን ሕጋዊ ሁኔታ አሟልቶ የኢንሹራንስ ሥራ እንደሚጀምር ታሳቢ በማድረግ በመሥራች ኮሚቴው በኩል የውጭ ኦዲተሮችን ተጋብዘው ነበር፡፡ ሰነድ ገዝተው ከነበሩት መካከል ሶስት ሰነድ አስገብተው የምሥረታ ወጪና

የአፐሬሽናል ኦዲት ለማድረግ በቀረበው ጨረታ ደገፋና ቴዎድሮስ የኦዲት አገልግሎት የኀብረት ሽርከና ማኀበር ማሸነፉ ይታወሳል፡፡ በተለያየ ምክንያት የኦፐሬሽን ሥራ ባለመጀመሩ በሚቀጥለው እ.ኤ.አ. ከሐምሌ ወር 2019 እንደሚጀመር ታሳቢ በመደረጉ ቀደም ሲል ለኦፐሬሽን ሥራው ዝቅተኛ ዋጋ የሰጠውንና በወቅቱ እ.ኤ.አ. ከጥር 2019 ጀምሮ ኩባንያውን ሥራ ለማስጀመር የነበረውን የምሥረታ ኮሚቴ እቅድ መሠረት በማድረግ ከአሸናፊው ጋር አመታዊ ሂሣብን ኦዲት ለማድረግ የሚያስከፍለን ዋጋ ላይ ድርድር ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም እንደገና ጨረታ ቢወጣ ሁሉንም ሂደት ለማከናወን ከአንድ ወር በላይ የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ወጪውን የሚያንርና የምሥረታ ጊዜውን የሚያራዝም በመሆኑ በነሐሴ ወር በነበረው ምዘና በዋጋና በአጠቃላይ ምዘና የተሻለ ለነበረው ደገፋና ቴዎድሮስ የኦዲት አገልግሎት የኀብረት ሽርከና ማኀበር የአመቱን ማለትም የ2011/12 በጀት አመት ኦዲት ቫትን ጨምሮ በብር 69,000/ስድሳ ዘጠኝ ሺህ/ ለመሥራት በመስማማቱ የፈራሚ ጉባዔው ውሳኔ እንዲሰጥበት የመሥራች ኮሚቴው ለፈራሚ ባለአክሲዮኖች ጉባዔ አቀረበ፡፡

በዚህ መሠረት ቀደም ሲል በቴክኒካልና በፋይናንስ ጥምር ምዘና የተሻለ ያመጣውን ደገፋና ቴዎድሮስ የኦዲት አገልግሎት የኀብረት ሽርከና ማኀበር ለ2011 ቀሪውን የምሥረታ ወጪ ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ እንዲሁም የ2012 በጀት ዓመትን  አመታዊ ሂሣብ እንዲመረምር የቀረበውን ዋጋና ምዘና መሠረት በማድረግ  የፈራሚዎች ጉባዔ ከላይ በቀረበው ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር 69,000/ስድሳ ዘጠኝ ሺህ/ እንዲሰራ ያለምንም ተቃውሞና ድምጸ ተአቅቦ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡

## 8. በማኀበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት የዲሬክተሮች ቦርድን መሾም

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 350/1/ እንደሚገልጸው የመጀመሪያዎቹ አስተዳዳሪዎች በማኀበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በማስተዳደሪያ ደንብ ለመመረጥ ይችላሉ ይኸው ምርጫ እንዲጸና መጀመሪያ አክሲዮን ለመግዛት ለፈረሙ ሰዎች ጉባኤ ይቀርባል፡፡ ይህ ምርጫ ያልጸና እንደሆነ ጉባኤው ሌሎች አስተዳዳሪዎችን ይመርጣል፡፡ በአንቀጽ 350/2/ ላይም ወደፊት የሚመረጡ አስተዳዳሪዎች በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ ሲል ይደነግጋል፡፡ በንኡስ አንቀጽ ሶስትም የአስተዳዳሪዎች ሹመት የሚጸናው ለሶስት አመት ብቻ ነው በማለት ስለሚደነግግ በዚህ መሠረት የመሥራች ኮሚቴው ከባለአክሲዮኖች መካከል በሥራና በሥራ አመራር  ልምድ፣ በአባላቱ የሙያ ስብጥር፣ ወደፊት ለኩባንያው ድማሬ

በሚያደርጉት አስተዋጽኦ፣ እንዲሁም የኋላ ታሪካቸውን በማጥናት ያቀረበ ሲሆን ምናልባት ከዘጠኙ ውስጥ በአካል የማይገኝ ካለ ሶስት ተጠባባቂዎች እንደተዘጋጁ ተገለጸ፡፡

በዛሬው እለት የቀረቡት ከዚህ ቀደም በነበረው የፈራሚዎች ጉባዔ ቀርበው በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት አግኝተው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ሆኖም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 350/5/ መሠረት ለእያንዳንዳቸው ድምጽ መስጠት እንዳለበት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሰጠው ማስተካከያ መሠረት በመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የቀረቡትን እጩዎች ጉባዔው አስተያየት እንዲሰጥባቸው ከቀረበለት በኋላ ሁሉንም እጩዎች በጉባዔው ፊት ቀርበው የትምህርትና የሥራ ልምዳቸውን በመግለጽ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ተደርጎ በስብሰባው ላይ በነበሩ ፈራሚዎች ተቀባይነት በማግኘታቸው ዘጠኙም በእጩነት ቀርበው ድምጽ እንዲሰጥባቸው ቀረቡ፡፡ ድምጽ እንዲሰጥባቸው የቀረቡት እጩዎች ስም ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

1. ኢንጅነር መልአኩ አዘዘው
2. ሻለቃ ጀእፋር ጊዲ አባ መጋል
3. አቶ ራቴነህ ፋሲል
4. ወ/ሮ ሜሮን ታደሰ
5. ወ/ሮ ዘለዓለም ፍስሐ
6. አቶ ሰለሞን መንግሥተአብ
7. አቶ ዮናስ አምደጽዮን
8. አቶ እሸቱ ወልደኪዳንን
9. ወ/ሮ ዮዲት ገብረትንሣኤ

ለባለአክሲዮኖችም በቀረቡት እጩዎች በየስማቸው አንጻር የድምጽ መስጫ ሳጥን ተዘጋጅቶ በስብሰባው ላይ በተገኙ ባለአክሲዮኖች ድምጽ እንዲሰጡ ተደረገ፡፡

ባለአክሲዮኖች ድምጽ ከሰጡ በኋላ ቆጠራው የሚወስደውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ባለአክሲዮኑ በጉባኤ ጽ/ቤት አባላት የድምጽ ቆጠራው በእለቱ ተካሂዶ የቆጠራው ውጤት በፕሮጀክት ጽ/ቤት ቢሮ በእለቱ ወይም በሚቀጥለው የሥራ ቀን እንዲለጠፍ ተስማምተው የጉባኤው

ቃለጉባኤ እንዲነበብና ጉባኤው እንዲቋጭ በመጠየቃቸው የጉባዔውን ቃለጉባኤ ወደማጽደቅ ተሸጋገረ::

## 9. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማፅደቅ

የስብሰባው ቃለ-ጉባዔ በጉባዔው ፀሐፊ ከተነበበ በኋላ ያለምንም ማሻሻያና ድምጸ ተአቅቦ በስብሰባው ላይ በተገኙ ፈራሚ ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምጽ ጸድቋል:: ስብሰባው ከቀኑ 6.45 ላይ ተጠናቀቀ::

መጋቢት 21/2011 አዲስ አበባ

**የጉባዔ ጽ/ቤት አባላት ስም** ፊርማ

1. አቶ አማረ ሀበ ....................
2. አቶ መስፍን አበበ /ከቱሉ ቶኩማ አ.ማ./ ....................
3. አቶ ኢሳያስ ተስፋየ /ከምናየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር/ ....................
4. አቶ ሰለሞን ደምሌ /ጸሐፊ/ ....................

**በጉባዔው የተገኙ የመሥራች ኮሚቴ አባላት**

1. አቶ አማረ ሀበ ....................
2. አቶ እሸቱ ወልደኪዳን ....................
3. አቶ ዮናስ አምደጽዮን ....................
4. አቶ ሹመቴ ዘርይሁን ....................

**መጋቢት 21/2011 ዓ.ም.**

የዘመን ኢንሹራንስ ፈራሚ ባለአክሲዮኖች መጋቢት 21/2011 ዓ.ም በኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ ሆቴል ከጠዋቱ 2.30 ጀምሮ ባካሄደዉ የፈራሚዎች ጉባዔ በእጩነት የቀረቡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የድምጽ ውጤት በአክሲዮን ብዛት ሲገለጽ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል

1. ኢንጅነር መልአኩ እዘዘው...........................13,004 አክሲዮኖች
2. ወ/ሮ ሜሮን ታደሰ...........................12,500 አክሲዮኖች
3. ወ/ሮ ዘለዓለም ፍስሐ...........................12,215 አክሲዮኖች
4. ሻለቃ ጃእፋር ጊዲ አባመጋል...........................11,109 አክሲዮኖች
5. ወ/ሮ ዮዲት ገብረትንሣኤ...........................10,853 አክሲዮኖች
6. አቶ እሸቱ ወልደኪዳን...........................10,757 አክሲዮኖች
7. አቶ ሰለሞን መንግሥተአብ...........................10,135 አክሲዮኖች
8. አቶ ራቴነህ ፋሲል...........................10,088 አክሲዮኖች
9. አቶ ዮናስ አምደጽዮን...........................10,019 አክሲዮኖች

ከላይ የተጠቀሱት ባለአክሲዮኖች በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ኩባንያውን እንዲመሩ በረቂቅ መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ተካተው የቀረቡና በተናጠል ተገቢው ድምጽ ድጋፍ ያገኙበት ውጤት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የቀረበው በፈራሚዎች ጉባዔ የጸደቀ ሲሆን በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚፈለገውን ተገቢ መስፈርት ያሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን እንገልጻለን፡፡

1. አቶ አማረ ሀበ የጉባኤው ሰብሳቢ...........................
2. አቶ መስፍን አበበ ድምጽ ቆጣሪ ከቱሉ ቶኩማ ንግድና ትራንስፖርት ኢ.ማ...........................
3. አቶ ኢሳያስ ተሰፋዬ ድምጽ ቆጣሪ ከምናየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር...........................
4. አቶ ሰለሞን ደምሌ የጉባኤው ጸሐፊ...........................

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ (ቅርንጫፍ ስምንት ጽ/ቤት)
ቁጥር 78/1437/[illegible]/12
በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል ።
አዲስ አበባ 05/05 ቀን 2012 ዓ.ም.

የሰነድ ሁኔታ ሰይፉ ተ/ሃይማኖት
ማረጋገጫና ምዝገባ ባለሙያ IV
Seyfu T/Haymanot
Document Authentication and
Registration Expert IV

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ (ቅርንጫፍ ስምንት ጽ/ቤት)
[illegible]
የአገልግሎት ዋጋ ብር 508
[illegible]
[illegible]
[illegible] ቁጥር 1632780
6/1[illegible] ቀን 20 12 ዓ.ም
[illegible]

Federal Documents Authentication & Registration Agency
Addis Ababa (Branch Eight Office)

# የዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር በመሥራቾች ጉባዔ የጸደቀ የመተዳደሪያ ደንብ

## አጠቃላይ ውሣኔዎች

እኛ የዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር /ከዚህ በኋላ ኩባንያ እየተባለ የሚጠራ/ባለአክሲዮኖች ቀጥሎ በሰፈሩት ውሳኔዎችና ድንጋጌዎች ለመተዳደር በሙሉ ፈቃደኝነት በመስማማት ይህ መተዳደሪያ ደንብ ኩባንያው ለሥራው አመራር የሚጠቀምበት ሕጋዊ ሰነድ እንዲሆን በሙሉ ድምጽ አጽድቀነዋል፡፡በተጨማሪም በዚህ ደንብ ሳይወሰን የመድን ሥራን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ፣ የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ የንግድ ሕግ እና ሌሎች ሕጐች በኩባንያው ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ተስማምተን አጽድቀናል፡፡

## አንቀጽ አንድ

### የመተዳደሪያ ደንቡ ወሰንና አፈጻጸም

1.1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ የኩባንያው መመሥረቻ ጽሑፍ አንድ አካል ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን በኩባንያው መሥራች አባላት የተዘጋጀና የኩባንያውን ሥራ የሚወሏን ነው፡፡

1.2. የቃሉ ትርጉም ሌላ አግባብ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተጠቀሱት ቃላትና አነጋገሮች በኢትዮጵያ ንግድ ሕግና የመድን ሥራን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይሆናል፡፡

1.3. በዚህ የመተዳደሪያ ደንብና የመመሥረቻ ጽሑፍ መካከል ልዩነት ካለ በመመሥረቻ ጽሑፍ የሚገኘው የበላይነት ይኖረዋል፡፡

1.4. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ያልተገለጹ ሁኔታዎች ቢኖሩ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣የመድን ሥራን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሁለት

### የኩባንያው አክሲዮኖች

2.1. የኩባንያው አክሲዮኖች አንድ ዓይነት ተራ እና በባለአክሲዮኖች ስም የተመዘገቡ አክሲዮኖች ይሆናሉ፡፡

2.2. ማናቸውም አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡

2.3. አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ሲሆኑ ከአንድ በላይ ሰዎች የአክሲዮኖች የጋራ ባለሀብት የሆኑ እንደሆነ የአክሲዮኖችን መብት የሚወከል የጋራ አንደራሴ መሾም ያለባቸው ሲሆን የጋራ ባለሀብቶች ከባለአክሲዮንነት የተነሳ ላሉት ግዴታዎች በአንድነት ሳይከፋፈል ኃላፊ ናቸው፡፡

2.4. ማንኛውም ባለአክሲዮን በስሙ የተመዘገበ የአክሲዮን የምስክር ወረቀት በቦርዱ ሊቀመንበርና በኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተፈርሞ የሚሰጠው ሲሆን የምስክር ወረቀቱም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 330 የተመለከቱትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት፡፡

2.5. ኩባንያው በዋናው መ/ቤቱ በስማቸው አክሲዮን ያላቸውን ሰዎች ዝርዝር የሚያመለክት መዝገብ ይይዛል፡፡

2.6. የኩባንያው አክሲዮን በአዳ መያዣነት ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የመያዣው ውል በኩባንያው መመዝገብ ያለበትና በአክሲዮኑ የምስክር ወረቀት ጀርባ የመያዣው ሁኔታ ተገልጾ በኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበርና በኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ መፈረም አለበት፡፡

2.7. አንድ አክሲዮን በመያዣ የተሰጠ እንደሆነ ተቃራኒ ስምምነት በባለአክሲዮኑና በመያዣ ተቀባዩ መካከል ከሌለ በስተቀር በባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች ድምጽ የመስጠት መብት በመያዣ የተቀበለው ይሆናል፡፡

2.8. ባለአክሲዮኖች ላልከፈሉት ገንዘብ ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በጥሬ ገንዘብ የሚወጣውን አዲስ አክሲዮን ለመግዛት ባላቸው አክሲዮን መጠን በተሰጠው የሽያጭ ጊዜም የቀዳሚነት መብት አላቸው፡፡

2.9. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ከተጣራው የዓመት ትርፍ ድርሻና ኩባንያው ማኅበሩ ሲፈርስ ከተጣራው ድርሻው በአክሲዮኑ ልክ የማግኘት መብት አለው፡፡

2.10. ማንኛውም ባለአክሲዮን በሕግ አግባብ ካልሆነ በስተቀር የባለአክሲዮንነት መብቱን ሊያጣ አይችልም፡፡

2.11. ማንኛውም ባለአክሲዮን የሰብሰባን የሥነሥርዓት ደንብ ተከትሎ በስብሰባዎች የመሳተፍ፣ድምጽ የመስጠትና የማግኘት፣ ተቃውሞ የማሰማት እንዲሁም ትርፍ የመካፈል መብት አለው፡፡

2.12. እያንዳንዱ አክሲዮን የአንድ ድምጽ መብት ያለው ሲሆን ባለአክሲዮኑም ባለው አክሲዮን መጠን ድምጽ የመስጠት መብት አለው፡፡

2.13. ማንኛውም ባለአክሲዮን በማንኛውም ጊዜ ሕግ የሚፈቅድለትን ሰነዶች የመመልከትና የዲሬክተሮች ቦርድን ሪፖርትና የኩባንያውን የሂሣብ መግለጫዎችና መዛግብት ግልባጭ በኩባንያው ወጪ የመቀበል መብት አለው፡፡

## አንቀጽ ሶስት

## የባለአክሲዮኖች ጉባኤዎች

### 3.1. ስለጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ድንጋጌዎች

3.1.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች መደበኛና ድንገተኛ ተብለው ይከፈላሉ

3.1.2. ጠቅላላ ጉባዔዎች እንዲሰበሰብ ጥሪን ለማድረግ የሚችሉት አስተዳዳሪዎች፣ ተቆጣጣሪዎችና ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በንግድ ሕጉ በተጠቀሰው መሠረት ቢያንስ ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ ሃያ በመቶ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ በጠየቁ ጊዜ ተቆጣጣሪዎች ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ ጥሪ ማድረግ አለባቸው፡፡

3.1.3. ጠቅላላ ጉባዔዎች በፖስታ አደራ ደብዳቤ ወይም በቀጥታ ለባለአክሲዮኑ መጨረሻ በሰጠው አድራሻ በማስፈረም በመላክ እንዲሁም በብዛት ታትሞ በሚወጣ ጋዜጣ በማውጣት ይሆናል፡፡

3.1.4. በማናቸውም ጉባዔዎች የጉባዔው አጀንዳ ከስብሰባው 15 ቀን በፊት ተዘጋጅቶ መላክ አለበት፡፡

3.1.5. ለእያንዳንዱ የጉባዔ አባል በጉባዔው ላይ ለመገኘት የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡

3.1.6. በማናቸውም ጉባዔ የቦርዱ ሊቀመንበር በስብሳቢነት የሚመራ ሲሆን የቦርዱ ሊቀመንበር በሌሉበት ጊዜ ጉባዔውን የቦርዱ ምክትል ሊቀመንበር ስብሰባውን ይመራል

3.1.7. ጉባዔው ሁለት ከፍተኛ አክሲዮን ድርሻ ካላቸው ባለአክሲዮኖች በድምጽ ቆጣሪነት የሚመርጥ ሲሆን የስብሰባው ጸሐፊ በጉባዔ ጽ/ቤት ይመድባል፡፡

3.1.8. የጉባዔው ውይይቶችና በስብሰባው የተነሱ ጉዳዮች በጽሑፍ ተመዝግበው በተገኙት ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ፊት በጸሐፊው ጠቅለል ብለው የሚነበቡ ሲሆን ቃለ ጉባዔው ለማስረጃነት እንዲሆን በቦርድ አባላትና በጉባዔው ጽ/ቤት አባላት ይፈረማል፡፡ የቃለጉባዔው ዝርዝር በንግድ ሕግ በተመለከተው መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡

3.1.9. የመጀመሪያው የጉባዔ ጥሪ ከአሥራ አምስት ቀን በፊት ሁለተኛው ከስምንት የሥራ ቀን ቀደም ብሎ መላክ አለበት፡፡

### 3.2. ስለድንገተኛ ጉባዔዎች

3.2.1. በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው

3.2.1.1. በኩባንያው መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ለውጥ ለማድረግ

3.2.1.2. ባለአክሲዮኖች በኩባንያው ባላቸው ገንዘብ/ካፒታል/ ላይ እንዲጨምሩ ለማድረግና የማስገቢያ ጊዜ ለመወሰን

3.2.1.3. የኩባንያውን መጠባበቂያ ገንዘብ በማግባት ዋናውን ገንዘብ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለመጨመር

3.2.1.4. ኩባንያው እንዲፈርስ ለመወሰን

3.2.1.5. ሌሎች ለድንገተኛ ጉባዔ በሕግና በብሔራዊ ባንክ የተሰጡ ስልጣኖች ናቸው፡፡

3.2.2. ካፒታል ጭማሪን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆነው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ሲወስን ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎች የድንገተኛ ጉባዔዎች ውሳኔዎች በጉባዔው የሚገኙ ድምጽ ያላቸው ሲያገኙም የድምጽ

መስጫ ወረቀቶች ቁጥር ውስጥ ሳይገቡ ከተሰጠው ድምጽ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ውሳኔዎቹን ሲያጸድቁ ነው

3.2.3. ከተጠቀሱት በስተቀር በድንገተኛ ጉባዔዎች የሚቀርቡ ጉዳዮች በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ድምጽ አሰጣጥና ኮረም ሁኔታዎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3.2.4. በድንገተኛ ጉባዔዎች በመጀመሪያ ጥሪ ተደርጎ የስብሰባው ኮረም ካልሞላ በአደራ ደብዳቤ አማካኝነት ለሁሉም ባለአክሲዮኖች ሁለተኛና ሶስተኛ ጥሪ በንግድ ሕጉ መሠረት ይደረጋል፡፡

3.3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች

3.3.1. የኩባንያው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣን ይኖረዋል

3.3.1.1. የኩባንያውን የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ ሂሣብ፣ የዲሬክተሮችና የኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ፣ተከራክሮበት ለማጽደቅ ወይም ላለመቀበል

3.3.1.2. የትርፉን አመዳደብና አከፋፈል እንዲሁም በጠቅላላው ባለፈው የሂሣብ ማጠቃለያ ሪፖርት ባሉት የሂሣብ ጉዳዮች በተመለከተ ውሳኔ መስጠት

3.3.1.3. የቦርድ ዲሬክተሮችንና ኦዲተሮችን መሾም፣ መሻር እና የሥራቸውን ዋጋ መወሰን

3.3.1.4. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 375 መሠረት የተመለከተውን ሪፖርት ከገመገመ በኋላ ሂሣቦችን ማስተካከል

3.3.1.5. የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን ባልሆኑ ጉዳዮች ሌሎች ጉዳዮች ላይ መወሰን

3.3.2. ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሂሣብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ውስጥ መጠራት አለበት

3.3.3. በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ድምጽ ብልጫና አስፈላጊው አነስተኛ የባለአክስዮኖች ቁጥር የሚከተለው ይሆናል፡፡

3.3.3.1. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ 25 በመቶ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው እንዲገኙበት ያስፈልጋል፣

3.3.3.2. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸው የአክሲዮኖች ቁጥር ማናቸውም ቢሆን የጉባዔው ውሳኔ የሚፀና ሲሆን የሚተላለፉት ውሳኔዎች ተራ በሆነ የድምጽ ብልጫ ሆኖ ስለ ድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ድምጽ ያልሰጡ ቢኖሩም እንዲሁም ድምጽ ያልተፃፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

3.3.4. በመጀመሪያው የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ኮረም ባለመሟላቱ ሁለተኛ ስብሰባ መደረግ ካለበት ሁለተኛው የስብሰባ ጥሪ በአደራ ደብዳቤ ለባለአክሲዮኖች በመላክና በብዛት በሚሰራጭ ጋዜጣ ጥሪ በማድረግ ይሆናል፡፡

3.3.5. የእያንዳንዱን ጠቅላላ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ትክክለኛ ቅጅ ቃለ ጉባዔው የሚመለከተው ስብሰባ በተደረገ በሃያ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይላካል፡፡

## አንቀጽ አራት
## የዲሬክተሮች ቦርድ

4.1. አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣

4.1.1. ኩባንያው በዘጠኝ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመራል፡፡

4.1.2. የመጀመሪያዎቹ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በኩባንያው የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ በመሥራች አባላት የሚሾሙ ሲሆን በተከታታይ የሚሾሙት የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሾማሉ፡፡

4.1.3. የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሦስት ዓመታት ብቻ እንዲያገለግሉ የሚመረጡ ቢሆንም የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ሆኖ መሠረት ለተጨማሪ ጊዜ ለማገልገል ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ከስድስት ዓመት በኋላ እንደገና ለመመረጥ ግን ቢያንስ ስድስት ዓመት መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

4.1.4. እያንዳንዱ የዲሬክተሮች ቦርድ አባል በስሙ ከተመዘገቡት አክሲዮኖች ውስጥ 10 አክሲዮኖች ለዋስትና ማስያዝ ያለበት ሲሆን እነዚህ አክሲዮኖች የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በሥራቸው ላይ እስከቆዩና በሥራቸው ወቅት ያለባቸውን ኃላፊነት እስከሚያወራርዱበት ጊዜ ድረስ በኩባንያው ተይዘው ይቆያሉ፡፡

4.1.5. የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የባአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስነው መሠረት ወርሃዊ ሆነ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ከኩባንያው ወጭ የሚታሰብ ሊከፈላቸው ይችላል፡፡

4.1.6. ማንኛውም ሰው የዲሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ በብሔራዊ ባንክ የወጣውን የመምረጫ መስፈርት ማሟላትና ምርጫው በብሔራዊ ባንክ ሊጸድቅለት ይገባል፡፡

4.1.7. የኩባንያው ማናቸውም የዲሬክተሮች ቦርድ አባል በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ በማናቸውም ጊዜ ከሥልጣኑ ሊወገድ ይችላል፡፡

4.1.8. የኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ለራሳቸው ወይም ለሦስተኛ ሰውም ፋንታ ቢሆን ከኩባንያው ጋር የውድድር ተግባር መሥራትና ከዘመን ኢንሹራንስ ኢ.ማ. በሚወዳደሩ ኩባንያዎች ወይም የንግድ ድርጅቶች ውስጥ አላፊነታቸው በአንድነትና ያልተከፋፈለ ከሆነ በዲሬክተሮች ቦርድ አባልነት መመረጥ አይችሉም፡፡

4.1.9. በኩባንያውና በዲሬክተሮች ቦርድ መካከል በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚደረገው ስምምነት ሁሉ የዲሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ ካልፈቀደ በስተቀር ስምምነቱ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4.1.10. ማናቸውም የዲሬክተሮች ቦርድ አባል ከኩባንያው ገንዘብ መበደር፣ ወይም የብድር አገልግሎት መቀበል ወይም ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ላሉባቸው እዳዎች ኩባንያውን ዋስ ማድረግ አይችልም፡፡

4.1.11. ኩባንያው በዋናው ጽ/ቤቱ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ በተደነገገው መሠረት የዲሬክተር ቦርድ አባላትን ዝርዝር የያዘ መዝገብ ማስቀመጥ አለበት፡፡

4.2. የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ውሳኔዎች፣

4.2.1. የኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በቦርዱ ሊቀመንበር እርሱ በሌለበት ጊዜ በቦርዱ ም/ ሊቀመንበር ወይም ሁለቱም ከሌሉ አባላት በሚወክሉት የዲሬክተሮች ቦርድ አባል ሊመራ ይችላል፡፡

4.2.2. የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቀደም ብሎ በስብሰባ በተወሰነው መሠረት ለሌላ ጊዜ የተላለፈ ስብሰባ ካልሆነ በስተቀር የስብሰባ ጥሪዎች በጽሑፍ ሆኖ የስብሰባውን አጀንዳ በመያዝ ከስብሰባው ሦስት ቀናት በፊት ለአባላት መተላለፍ አለበት፡፡

4.2.3. በኩባንያው መመሥረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካልተወሰነ በስተቀር የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ከመካከላቸው አንድ የቦርድ ሊቀመንበርና ም/ሊቀመንበር ይመርጣሉ፡፡

4.2.4. ቦርዱ የመረጠውን ሊቀመንበር ወይም ም/ሊቀመንበር ሊሽር ይችላል፡፡

4.2.5. ቦርዱ ለስብሰባው ፀሐፊ የሚመርጥ ሲሆን የኩባንያው ማናቸውንም ሠራተኛ በቦርዱ ስብሰባ እንዲገኝ ለማድረግ ይችላል፡፡

4.2.6. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የቦርድ አባል ሆኖ የማይመረጥ ሲሆን በዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ድምጽ ሳይሰጥ በአስረጅነት ሊገኝ ይችላል፡፡

4.2.7. የቦርድ ዲሬክተሮች ስብሰባ ለማካሄድ የሚቻለው ከቦርድ አባላት አብዛኛዎቹ ሲገኙ ብቻ ሲሆን በስብሰባዎች ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው ፍጹም በሆነ ድምጽ ብልጫ ነው፡፡ አንድ ሰው በእንደራሴነት የሚሰጠው ድምጽ ለአንድ የቦርድ አባል ብቻ ይሆናል፡፡

4.2.8. የቦርዱ ስብሰባዎች ውሳኔ በቃለ ጉባዔ መዝገብ ተመዝግቦ በስብሰባው በተገኙ አባላትና በፀሐፊ መፈረም አለበት፡፡

4.3. የዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣናትና ተግባራት፣

4.3.1. የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የኩባንያውን ሥራ በጋራ የመምራት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በአጠቃላይ የኩባንያውን አስተዳደር በጥንቃቄ ለመምራት ግዴታ አለባቸው፡፡

4.3.2. የዲሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በኩባንያው መመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችና የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

4.3.3. የኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ በተጨማሪ የሚከተሉትን ሥልጣን በተግባር ያውላሉ፡፡

4.3.3.1. የኩባንያውን ዋና ሥራ አስፈጻሚና ም/ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች መሾምና መሻር፣ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሉሥራውም ከፍያን መወሰን፣

4.3.3.2. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚያቀርባቸውን ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ የኩባንያውን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር ማጽደቅና የሥራ ሁኔታዎችን መወሰን፣

4.3.3.3. የኩባንያውን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሠራተኛች ጥቅማ ጥቅሞች፣ የኩባንያውን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ማጽደቅ፣

4.3.3.4. የኩባንያው ስም ስለሚከፈቱ የባንክ ሂሳቦች ፈራሚዎችን መወከል፣

4.3.3.5. የኩባንያውን የአስተዳደርና የስብሰባዎችን መደበኛ ሰነዶች እንዲያዙ ማድረግ፣

4.3.3.6. ሕግ በሚያዘው መሠረት የኩባንያውን የሂሣብ ሰነዶች መዛግብት እንዲያዝ ማድረግ፣

4.3.3.7. የኩባንያውን ሂሳቦች እንዲመረምሩ ለኩባንያው ኦዲተሮች ማቅረብ ለባለአክሲዮኖች ስብሰባዎች ስለኩባንያው እንቅስቃሴዎች የሂሣብ መግለጫዎች ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ፣

4.3.3.8. የኩባንያው ሦስት አራተኛ ካፒታል የጠፋ እንደሆን የኩባንያውን ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባኤ ሳይዘገይ መጥራት፣

4.3.3.9. በሕግና በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መያዝ ያለባቸውን መጠባበቂያ ገንዘቦች እንዲደራጁ ማድረግ፣

4.3.3.10. ኩባንያው ዕዳ መክፈሉን የተወ እንደሆነ ከገንዘብ ጠያቂዎች ጋር የመጠበቂያ ስምምነት እንዲደረግ ወይም ኩባንያው እንዲፈርስ እንዲወሰን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ማቅረብ፣

4.3.3.11. የመድን ሥራ አዋጅ እንደተጠበቀ ሆኖ በኩባንያው ስም በዋስትናም ሆነ ያለ ዋስትና ገንዘብ መበደርና በኩባንያው ስም የብድር ስምምነቶች፣ ውሎች የተሰፋ ሰነዶች የሚፈርሙትን ኃላፊዎች መወከል፣

4.3.3.12. የኩባንያውን ገንዘቦች የብሔራዊ ባንክና የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግባር ላይ ማዋል፣ወጪዎች ማጽደቅ እንደአስፈላጊነቱ ከተገባበት የኢንቨስትመንት መውጣት

4.3.3.13. የኩባንያውን ቋሚ ንብረቶችና ሀብቶች መሸጥና ማስተላለፍ፣ በኩባንያው ስም ሆነው የስም ማዘዋወር ተግባራትን የሚያከናውኑ ኃላፊን መወከል፣

4.3.3.14. የኩባንያው አመራር ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የጠለፉ ዋስትና ድርጅቶች ጋር ተነጋግሮ ያቀረበውን የጠለፋ ዋስትና ማየትና ይህንኑ እንዲያፀድቅ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ፣

4.3.3.15. በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ለዲሬክተሮች ቦርድ የተሰጡ ኃላፊነቶችን መወጣት

4.3.3.16. በማናቸውም ባለአክሲዮኖች ጉባዔዎች እንዲያከናውኑ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ማከናወን፣

## አንቀጽ አምስት

## ዋናው ሥራ አስፈጻሚ

5.1. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የኩባንያውን ሥራ ለመምራት ዋና ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን ዋና ሥራ አስፈጻሚው በኩባንያው ዲሬክተሮች ቦርድ አጠቃላይ አመራር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

5.1.1. ኩባንያውን በግል ድርጅቶች መንግሥታዊ አካላት ዘንድ መወከል፣

5.1.2. ለቦርድ ተጠሪ ከሆኑና ከምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች በስተቀር ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ የኩባንያውን የሥራ ኃላፊዎች በመምረጥ በዲሬክተሮች ቦርድ ሹመታቸውን ወይም መሻራቸውን ለቦርድ አቅርቦ እንዲፀድቅ ማድረግ፣

5.1.3. ቦርዱ ባወጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መሠረት የኩባንያው ሌሎች ሠራተኞች መቅጠርና ማሰናበት፣

5.1.4. በዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች መሠረት ሰነዶችን፣ ደብዳቤዎችን፣ ደረሰኞችን፣ ቼኮችን፣ የተሰፋ ሰነዶችን፣ የሐዋላ ወረቀቶችን፣ የጉምሩክ ዲክለራሲዮኖችን፣ ስምምነቶችን መፈረም፣

5.1.5. ስለ ኩባንያው አስተዳደር፣ የሥራ እንቅስቃሴና የፋይናንስ ሁኔታ በየጊዜው ለዲሬክተሮች ቦርድ እንደ ሥራው ባህርይ በየወሩ ወይም በየሩብ ዓመቱ ሪፖርቶች ማቅረብ፣

5.1.6. በኩባንያው ስም ወኪሎች፣ የሕግ አማካሪዎች፣ ነገረ ፈጆች ጠበቆች በመሾም የውክልና ሥልጣን መስጠት፣

5.1.7. የኩባንያውን እለታዊ ሥራዎች ማስተዳደርና መከታተል፣

5.1.8. ሥልጣኑን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለኩባንያው ሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ማስተላለፍ፣

5.1.9. የኩባንያውን በጀት፣ የሥራ እቅዶችና የሥራ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ለቦርዱ ዲሬክተሮች ማቅረብና ሲፈቀድ በሥራ መተርጎም፣

5.1.10. የዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎች መፈፀምና በቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን፣

5.1.11. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመድን ሥራ ፈቃድ ስለመደነገግ በተሰጠው ሥልጣን ለሌሎች ሕጋዊ አካላት የሚፈለጉትን ሪፖርቶችና መግለጫዎች ማስተላለፍ፣

5.2. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ብቃት በተመለከተ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5.2.1. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈሚም ሆነ ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሥራ አስኪፈጻሚነት ስለሚያበቁ ሁኔታዎች የሚያወጣውን መመሪያ ማሟላት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## ስለ ኩባንያው ሂሣብ

6.1. ኩባንያው የንግድና ሂሣብ መዛግብቱን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎችና ሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት መያዝ አለበት፡፡

6.2. ኩባንያው በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት መዝጊያ የንብረቱን፣ የሀብቱንና የዕዳውን ዝርዝር የሚመለከቱ ሰነዶች ማዘጋጀት አለበት፡፡

6.3. የኩባንያው የዳሬክተሮች ቦርድ ከአለፈው የሂሳብ ዓመት የታየውን የሂሣብ ሚዛን፣ የኪሳራና የትርፍ ሂሳብ ማጠቃለያ እንዲሁም ስለ ኩባንያው ሁኔታና አሠራር ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

6.4. የኩባንያው የሂሣብ ሪፖርት የኪሣራውንና የትርፉን ሂሣብ የሚገልፅ ዝርዝር የያዘና የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትና ኦዲተሮች በጠቅላላው የሚያገኙትን የሥራ ዋጋ የሚያመለክት ትክክለኛ ማስረጃ ያዘለ እንደሆንና ስለትርፍ አከፋፈልም የቀረበው የውሣኔ ሃሣብ እንዲኖርበት ያስፈልጋል፡፡

6.5. በኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድና በዋናው ሥራ አስፈጻሚ የተፈረሙ የሂሣብ መግለጫዎች የሚመለከተው ዓመት ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ዘንድ ተቀማጭ መሆን አለበት፡፡

6.6. የኩባንያውን የሥራ ሁኔታ የሚመለከቱና ለባለአክሲዮኖች ስብሰባ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ግልባጭ ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መተላለፍ አለበት፡፡

6.7. ከኩባንያው ከዓመቱ የተጣራ ትርፍ አሥራ አምስት በመቶ (15 በመቶ) ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ገቢ የሚያደርግ ሲሆን የዚህ ሂሣብ መጠን ከኩባንያው ዋና ገንዘብ መጠን ጋር እኩል ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ በሚወስነው መጠን ሌላ የመጠባበቂያ ሂሣብ ይይዛል፣

6.8. ኩባንያው የሂሣብ ዓመት ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ በሰላሣ ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ የዋለውን ሀብት፣ የተካባች ገንዘቦች ሁኔታና ለውጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያቀርባል፡፡

6.9. ኩባንያው ለየመድን ሥራ አይነቶች የተመለከተ ሂሳቦችና ተካባች ገንዘቦች እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

6.10. ኩባንያው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መጠባበቂያ ሂሣቦች ይይዛል፣

6.10.1. የውል ጊዜው ያላለቀ ነገር ግን ለተሰበሰበ አረቦን፣

6.10.2. ለተጠየቀ የካሣ ክፍያ ነገር ግን ላልተከፈለ የመድን ውል ተቀባዮች ጥያቄ፣

6.10.3. በመድን ውሉ መሠረት የክፍያ ግዴታን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተፈፅመው ነገር ግን የክፍያ ጥያቄ ላልቀረበባቸው ጉዳዮች፣

6.10.4. የጠለፋ ዋስትና በበቂ ሁኔታ ለማይሸፍናቸው የዋስትና ግዴታዎች

6.10.5. ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ለሚወስናቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች፣

6.11. የኩባንያው የተጣሩ ትርፎች የሚባሉት የኩባንያው ካሣ ከፍያዎች፣ በብሔራዊ ባንክ የተፈቀዱ የካሣና አረቦን መጠባበቂያዎች፣ ጠቅላላና አስተዳደራዊ ወጭዎች እንዲሁም አላቂ ለሚሆኑት ነገሮች መተኪያ ገንዘብና የገንዘብ ሰንቆች ሁሉ በሂሣብ ማጠቃለያው ጊዜ ከተገኙ ጠቅላላ ገቢዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚገኙት ትርፎች ናቸው፡፡ የሚከፈለውም ትርፍ በሂሣቡ ማጠቃለያ ጊዜ ከተገኘው ትርፍ ላይ በቅድሚያ ኪሣራዎች ከተቀነሱ በኋላ እንዲሁም በፊት ታስበው ያልተከፋፈሉ ትርፎችና አስፈላጊም ቢሆን ጠቅላላ ጉባዔው በተለይ ከመጠባበቂያ ገንዘብ ላይ ተነስተው በሂሣብ ማጠቃለያ ጊዜ የተገኘው ትርፍ ላይ ከተጨመረ በኋላና ሕጋዊ መጠባበቂያና በባለአክሲዮኞች ጠቅላላ ጉባዔ ተጨማሪና የተፈቀደ ሌላ የመጠባበቂያ ሒሳብ ተቀንሶ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## ኦዲተሮች

7.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ መደበኛ ጉባዔ የኩባንያውን ኦዲተሮች ይሾማል፣ይሽራል፣ ኦዲተሮቹ ለሦስት ዓመት ጊዜ እንዲያገለግሉ የሚሾሙ ሲሆን የብሔራዊ ባንክና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጐች እንደተጠበቁ ሆነው እንደ አስፈላጊነቱ ለተጨማሪ ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

7.2. ኦዲተሮች የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናሉ፣

7.2.1. የኩባንያውን መዛግብትና የገንዘብ የዋስትና ሰነዶችን መመርመር፣

7.2.2. የኩባንያውን የንብረት ዝርዝር መዝገብና የሂሣብ ሚዛኖች፣ የኪሣራውንና የትርፍ ሂሣብ በደንብና በእውነተኛ አሠራር መሠረት መሰራቱን፣

7.2.3. በኩባንያው ውስጥ የሚገኙ ስምምነቶችን ውሎችን፣ የሂሣብ መዛግብትን፣ ሰነዶችን፣ ቃለ-ጉባዔዎችን ሌሎችንም መዛግብትን ሁሉ እንዲቀርቡላቸው በመጠየቅ የመቆጣጠርና ምርመራ ማካሄድ፣

7.2.4. የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የኩባንያው ሁኔታ በሚገባ የሚያንፀባርቅ ለመሆኑ ማረጋገጥ፣

7.2.5. በየዓመቱ ለሚሰበሰበው ጠቅላላ ጉባዔ የሥራቸውን ውጤት የሚገልጽ ሪፖርት በጽሑፍ ማቅረብና በዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ተገቢ መስለው ያገኙአቸውን ማስገንዘቢያዎች ማመላከት፣

7.2.6. በጠቅላላ ጉባዔው የኩባንያውን ሂሣቦች በሙሉ እንዲያፀድቀው ወይም የመጠባበቂያ ጨምሮ እንዲያፀድቀው ወይም ውድቅ አድርጐ ወደ ዲሬክተሮች ቦርድ እንዲላክ ሃሳብ ማቅረብ፣

7.2.7. ስለትርፍ አከፋፈል በዲሬክተሮች ቦርድ በቀረበው ሃሳብ ላይ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ሆኖም ይህ ሃሳብ በኦዲተሮች ካልተደገፈ ጠቅላላ ጉባኤው በሂሣብ ሚዛኑ ላይ ሃሣብ ለመስጠት አይቻልም፡፡

7.2.8. መደበኛ በሆነ አሠራር የተሰሩትን ወይም የተጣሱ ጉዳዮችን ለዲሬክተሮች ቦርድና ለጠቅላላ ጉባዔ ማሳወቅና በሕግ የተከለከለ ወንጀል መሠራቱን ሲያውቁ ለዐቃቤ ሕግ ማሳወቅ፣

7.3. ኦዲተሮች የኩባንያውን ሂሣብ በሚመረምሩበት ወቅት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኦዲት ሥነምግባር ደንብ በሚጠይቀው መሠረት የተደነገገው ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን የሙያ ሥራ ሚስጥር ካወጡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ በኦዲተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7.4. ኦዲተሩ የመድን ሥራ አዋጅ ስለኦዲተሮችና ማስተካከያ እርምጃዎች በተደነገገው መሠረት እንደችግሩ ደረጃና በሕግ አግባብ ለኩባንያው አስተዳዳሪዎች፣ ለአቃቤ ሕግ ወይም ለብሔራዊ ባንክ ማስታወቅ ይጠበቅበታል፡፡

7.5. ኦዲተሮች የሪፖርቱን ኮፒ የሂሣብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በዘጠና ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ባንክ መላክ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## ምግዚት የኩባንያው መፍረስና ሂሣብ ማጣራት

8.1. ኩባንያው በሚከተሉት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡፡

8.1.1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኩባንያውን የመድን ሥራ ፈቃድ ከሰረዘና ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ ኩባንያው እንዲፈርስ ከተወሰነ፣

8.1.2. የኩባንያው የንግድ ሥራዎችና ዓላማዎች ሊከናወኑ የማይቻል ከሆነ፣

8.1.3. በባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጉባዔ ኩባንያው እንዲፈረስ ከተወሰነ፣

8.1.4. ከባለአክሲዮኖች አንዱ ባቀረበው ብቁ በሆነ ምክንያት ኩባንያው እንዲፈርስ ፍርድ ቤት ካዘዘ፣

8.1.5. ኩባንያው የመክሰር ውሣኔ እንዲሰጥለት ለፍርድ ቤት ከጠየቀ፣

8.1.6. ከኩባንያው ዋና ገንዘብ ሶስት አራተኛው ከጠፋ፣

8.1.7. ከመድን ሥራ አዋጅ ጋር ተያይዞ ስለምግዚትና መፍረስ በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሠረት

8.2. ኩባንያው ሲፈርስ ሂሣቡን የሚያጣሩት ሂሣብ አጣሪዎች ተግባራቸውን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የመመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎች

9.1. የባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጉባዔ ይህን መመሥረቻ ጽሑፍና የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል ይችላል፡፡

9.2. የባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጉባዔ የኩባንያውን መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ በሚያሻሽልበት ጊዜ የስብሰባው ሂደትና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና አግባብ ባላቸው ሕጐች በተደነገገው መሠረት ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ አሥር

## ተፈጻሚ የሚሆኑት ሕጐች

የኩባንያው መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ፣ ከመድን ሥራ ለመደንገግ ከወጣው አዋጅ፣ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እንዲሁም እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተመለከተው መሠረት በመስማማት ይህ የኩባንያው የመተዳደሪያ ደንብ በባለአክሲዮኖች የፈራሚዎች ጉባዔ የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔን ሥርዓት ተከትሎ ካጸደቀው በኋላ የተፈረመ ሲሆን መተዳደሪያ ደንቡ በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አግኝቶ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ይህ ሰነድ ..............................ወር..............ቀን 20..........ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ ተፈረመ

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

Federal Documents Authentication & Registration Addis Ababa

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ (ቅርንጫፍ ስምንት ጽ/ቤት)
ቁጥር ቀ8/2023/4ሀ/12
በጽሕፈት ቤቱ ተፈርሞ [illegible] ::
አዲስ አበባ 24/04 ቀን 2012 ዓ.ም.

ሽመልስ አዳሙ ዐጋ
የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ
ባለሙያ IV

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Eight Office)
የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ (ቅርንጫፍ ስምንት ጽ/ቤት) አዲስ አበባ

6180
2818 [illegible]

# ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር
# በፈራሚ ባለአክሲዮኖች የጸደቀ
# መመሥረቻ ጽሑፍ

መጋቢት 21 ቀን 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

Authentication Federal Documents & Registration Agency Addis Ababa (Branch Eight Office)
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
52

CamScanner

# ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኀበር

## የመመሥረቻ ጽሑፍ

### አንቀጽ አንድ

### የባለአክሲዮኖች ስም፣ዜግነት፣ አድራሻና የአክሲዮን ይዞታ

እኛ ስማችን፣ ዜግነታችንና አድራሻችን ከዚህ በታች የተገለጸው በርካታ ሰዎች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የመድን ሥራን ለመደንገግ ባወጣው አዋጅ ቁጥር 746/2004፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች፣ በ1952 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግና የዚህም ጽሑፍ አካል በሆነውና ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚተዳደር የመድን ሥራ የሚሰራ አክሲዮን ማኀበር ለማቋቋም ስለተስማማን "ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኀበር"ን ከዚህ በኋላ "ኩባንያ" ተብሎ የሚጠራውን ለመመሥረት በመወሰን፣የኩባንያውን ካፒታል ለማዋጣትና በየስማችን አቅጣጫ የተመለከተውን የአክሲዮን ብዛት ለመግዛት ቃል መግባታችን እናረጋግጣለን፡፡

Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Eight Office)

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## አንቀጽ ሁለት

## መጠሪያ

የማኅበሩ ስም "ዘመን ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር" ነው

## አንቀጽ ሶስት

## ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፎች

3.1. የኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣ የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23029/1000 ስልክ ቁጥር 0115575464/ 0115575850 የፋክስ ቁጥር.............ሆኖ አድራሻው በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር አዲስ ሲሆን አድራሻው እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል፡፡

## አንቀጽ አራት

## የአክሲዮን ማኅበሩ ዓላማዎች

የኩባንያው የንግድ ዓላማዎችና ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው

4.1. ማንኛውንም በጠቅላላ መድን ዋስትናዎች ውስጥ የሚካተቱ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች መስጠት

4.2. የኩባንያውን ዓላማዎችና የንግድ ሥራዎች በሚያጠናክሩና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲሰሩ በሕግ የተፈቀዱ ማንኛውም የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራዎችን መሳተፍ

## አንቀጽ አምስት

## ዋና ገንዘብ /ካፒታል/

5.1. በባለአክሲዮኖች የተፈረመው የካፒታል መጠን ብር 114,605,000/አንድ መቶ አሥራ አራት ሚሊዩን ስድስት መቶ አምስት ሽህ ብር/ ነው፡፡

5.2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 5000/አምስት ሽህ/ ዋጋ ባላቸው 22921/ ሃያ ሁለት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሃያ አንድ / ተራና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

5.3. ከተፈረመው አክሲዮን ውስጥ ብር 81,540,000/ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሽህ ብር/ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

5.4. የተፈረመው ካፒታል ውስጥ ቀሪ ቢኖር ኩባንያው የፈራሚ ባለአክሲዮኖች ስብሰባ ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ በአሥራ አምስት ወር ውስጥ ተከፍሎ ማለቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## አክሲዮኖች

6.1. የኩባንያው አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው አንድ ዓይነትና ልዩ መብት የማይሰጡ ተራ አክሲዮኖች ናቸው

6.2. በኩባንያው ውስጥ በዓይነት የሚከፈል አክሲዮን የለም

## አንቀጽ ሰባት

## የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ

7.1. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የትርፍ ክፍፍሉ የኩባንያው ኦዲተሮች ከመረመሩትና የዲሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካጸደቀው በኋላ ከተጣራው ትርፍ ላይ ተገቢው ታክስ ፣ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ፣ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉት ኪሣራዎችና ሌሎች ተቀናሾች ከተቀነሱ በኋላ በአንድ ጊዜ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7.2. ትርፍ ለባለአክሲዮኖች በሚከፋፈልበት ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታሳቢ ይሆናሉ

7.2.1. ከተከፈለው ጠቅላላ ካፒታል ውስጥ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለው የተከፈለ ካፒታል መጠን እና

7.2.2. በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአክሲዮኖች ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሎ በኩባንያው እጅ የቆየበት ጊዜ ናቸው

### አንቀጽ ስምንት

### ለመሥራቾች የተመደበ ትርፍ

8.1. ሀ/ በንግድ ሕግ አንቀጽ 307 /2/ መሠረት በመጀመሪያ ለፈረሙና በሙሉ የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ላዋጡ አባላት አሥር በመቶ ለ/ በአንቀጽ 307 /3/ በሚቋቋመው አክሲዮን ማኅበር ገንዘባቸውን ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን መስዋእት በማድረግ በአክሲዮን ማኅበሩ ምሥረታ ወቅት የማደራጀት ሥራውን እውን ላደረጉትና የመግለጫ ጽሑፍ ላይ ስማቸው ለሰፈረው አምስት ግለሰቦች አሥር በመቶ ለሶስት ዓመት የሚቆይ የመሥራችነት ጥቅም ይከፈላቸዋል፡፡

8.2. በዚህ አንቀጽ 8.1 የተጠቀሰውና ለመሥራቾች የሚመደበው ትርፍ ክፍያ ኩባንያው ማትረፍ ከጀመረበት የበጀት ዓመት ጀምሮ ከመጀመሪያዎቹ የሶስት ዓመታት የተጣራ ትርፍ ላይ ይሆናል፡፡

### <u>አንቀጽ ዘጠኝ</u>

### <u>የአስተዳደር አካላት</u>

9.1. የኩባንያው አስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸው

9.1.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

9.1.2. የዲሬክተሮች ቦርድ

9.1.3. ኦዲተሮች

9.2. ከላይ የተመለከቱት የኩባንያው አስተዳደር አካላት ሥልጣንና ኃላፊነት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግና በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ አሥር
### የባለአክሲዮኖች ጉባዔዎች

10.1 የባለአክሲዮኖች ጉባዔ የሚያካሂዳቸው የተለያዩ ስብሰባዎች ዓይነት፣ የስብሰባ ጥሪ፣ የድምጽ ብልጫና ኮረም፣የጉባዔዎች ሥልጣንን በተመለከተ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

10.2.የጉባዔው ዓይነትና የአጀንዳ ነጥቡ ሕግ የሚጠይቀው ምልዓተ ጉባዔ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው ባለአክሲዮኖችን በመወከል በስብሰባ ባልተገኙት፣ በሃሣብ በተለዩት፣ መምረጥ ባልቻሉት ወይም የመምረጥ መብት በሌላቸው ወገኖች ስም ጭምር የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

### አንቀጽ አሥራ አንድ
### የዲሬክተሮች ቦርድ

11.1. የኩባንያው የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ብዛት ዘጠኝ ይሆናል፡፡

11.2. የሚከተሉት ባለአክሲዮኖች የኩባንያው የመጀመሪያው የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በመሆን ለሶስት ዓመታት ያገለግላሉ፡፡ 11.2.1 ኢንጅነር መልአኩ እዘዘው. 11.2.2. ሻለቃ ጃእፋር ጊዲ አባመጋል 11.2.3. ወ/ሮ ዮዲት ገብረትንሣኤ 11.2.4. ራቴንህ ፋሲል. 11.2.5. ሰለሞን መንግሥተአብ 11.2.6 ወ/ሮ ሜሮን ታደሰ 11.2.7. ወ/ሮ ዘለአለም ፍስሐ 11.2.8 ዮናስ ኡቁበእዝጊ 11.2.9 እሸቱ ወልደኪዳን

11.3. የኩባንያው ዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር፣አመዳደብ፣ ከሥልጣን መሻርና መወገድ፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሁኔታና ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

11.4. የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ም/ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች በዲሬክተሮች ቦርድ ይሾማሉ፣ ይሻራሉ፡፡ ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች አመራር አባላት በዋና ሥራ አስፈጻሚ ቀርበው በዲሬክተሮች ቦርድ ይጸድቃል፣ መሻሪያ ሲቀርብ ያጸድቃል፡፡

11.5. የዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች የሥራ ኃላፊነት በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ መሠረትና ብሔራዊ ባንክ ስለከፍተኛ ሥራ አመራሮች ባወጣው መመሪያና ሌሎች ሕጐች መሠረት በማድረግ ይፈጸማል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## ኦዲተሮች

12.1. የኩባንያው ኦዲተሮች ሹመት፣ ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሶስት
## ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

13.1. በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንቡ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በንግድ ሕግ በተደነገገውና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ይሆናል

13.2. የኩባንያው ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 7 መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አራት
## ማስታወቂያዎች

14.1. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

14.2. ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኑ የሚተላለፈው በአስመዘገበው አድራሻና እንደአመቺነቱ በፖስታ፣ በመልእክተኛ፣ በፋክስ፣ በኢሜይል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አምስት
## ኩባንያው ተቋቋሞ የሚቆይበት ጊዜ

15.1. ኩባንያው የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስድስት
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

16.1. ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል፡፡

16.2. በሌላ ቋንቋ የተጻፈ የመመሥረቻ ጽሑፍ ቅጅና የአማርኛ ቅጅ በሚጣረስበት ጊዜ የአማርኛ ቅጅ ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

16.3. ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በፈራሚዎች ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አግኝቶ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ይህ የመመሥቻ ጽሑፍ ዛሬ ቀን ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተፈረመ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK
Federal Documents Authentication & Registration Agency Addis Ababa (Branch Eight Office)

በፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ (ቅርንጫፍ ...)

ቁጥር 78/2022/4U/12

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል ::

አዲስ አበባ 24/04 ቀን 2012 ዓ.ም

ሽመልስ አዳሙ

የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ባለሙያ IV

Federal Documents Authentication & Registration Agency (Branch) Addis Ababa

6580

29/9/1508992

U5